የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ – ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 47
ADDIS ABABA – 28th June 2004


ማውጫ


የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፮/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ ለማስፈጸም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፮/፲፱፻፺፮ ዓ.ም ...................... ገጽ ፪ሺ፮፻፵፩


CONTENTS


Council of Ministers Regulation No. 106/2004
Coucils of Ministers Regulation No. 106/2004 to Provide for the implementation of Cooperative Societies Proclamation No.147/1998. ... Page 2641


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፮/፲፱፻፺፮

## ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ አፈጻጸም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ አንቀጽ ፶፱ እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ ለማስፈጸም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፮/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፤

፩) "አዋጅ" ማለት የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ ነው።

፪) "መደበኛ ስብሰባ" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፺፩ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚደረግ ጠቅላላ ጉባዔ ማለት ነው።

፫) "የኅብረት ሥራ ማኅበር" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፪(፪) የተጠቀሰው ትርጉም ይኖረዋል ።

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 106/2004*

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE IMPLEMENTATION OF COOPERATIVE SOCIETIES PROCLAMATION*

This Regulation is issued by the council of Ministers pursuant to article 5 of the definition of powers and Duties of the Executive organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation NO.4/1995 and article 59 of Cooperative Societies Proclamation No.147/1998.

### SECTION ONE
### *General*

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as "Coucils of Ministers Regulation No. 106/2004 to Provide for the implementation of Cooperative Societies Proclamation No.147/1998."

2. *Definition*

In this Regulation, unless the context requires otherwise.

1/ "Proclamation" means cooperative societies Proclamation No. 147/1998.

2/ "Regular meeting" means a general assembly convened pursuant to sub article 1 of article 22 of proclamation No 147/1998

3/ "Cooperative society" Means an entity that has got a definition referred to (indicated) under article 2(2) of the proclamation.

፬) "አግባብ ያለው ባለሥልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፪፻፸፬/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፪(፩) መሠረት የተቋቋመ የኅብረት ሥራ ኮሚሽን እና በየክልሉ የተቋቋሙ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮዎችና ጽሕፈት ቤቶችን ይጨምራል ፡፡

፭) "ኅብረት" (ዩኒየን) ማለት ከአንድ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኅብረት ነው ፡፡

፮) "ፌዴሬሽን" ማለት ከአንድ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ኅብረቶች (ዩኒየኖች) እና የሕብረት ሥራ ማኅበራት ስብስብ ነው ፡፡

፯) "ሊግ" ማለት የኅብረት ሥራ ማኅበራት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚመሠርቱት የኢትዮጵያ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሊግ ነው ፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበራት አመሠራረት

፫· *የመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አመሠራረት*

፩) መሠረታዊ ማኅበር በተወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ወይም በሚሠሩ ወይም በተወሰነ ሙያ በተሰማሩ ፈቃደኛ ግለሰቦች ይቋቋማል። የመሥራች አባላት ቁጥር ከአሥር አያንስም ፡፡ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ከኢኮኖሚያዊ ብቃት አኳያ ተመልክቶ የአባላትን መነሻ ቁጥር ለመወሰን የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል ፡፡

፪) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚመሠረት መሠረታዊ ማኅበር የሥራ ክልል በአንድ ክልል ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን የሚሸፍን ሊሆን ይችላል ፡፡

፫) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፪ በተመለከተው የሥራ ክልል ውስጥ ከአንድ በላይ የተለያዩ ዓይነቶች መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሊመሠረቱ ይችላሉ።

፬· *የኅብረት ሥራ ኅብረት (ዩኒየን) አመሠራረት*

፩) የዚህ ሕግና ሌሎች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የሚመለከቱ ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተመሣሣይ ዓላማ ያላቸው መሠረታዊ ማኅበራት የሕብረት ሥራ ኅብረት (ዩኒየን) ሊመሠረቱ ይችላሉ።

፪) በዚህ ሕግና በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቁ ሆነው ከኅብረቱ ጋር ተመሣሣይ ተግባር የሚያከናውንና የማኅበሩን መርሆች የተቀበለ ግለሰብ የኅብረቱ (ዩኒየን) አባል ሊሆን ይችላል።

፭· *የኅበረት ሥራ ፌዴሬሽን አመሠራረት*

፩) የዚህ እና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተመሣሣይ ዓላማ ያላቸው ኅብረቶች በፌዴራል ደረጃ ፌዴሬሽን ሊመሠርቱ ይችላሉ ፡፡

፪) የዚህ እና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከፌዴሬሽኑ ጋር ተመሣሣይ ተግባር የሚያከናውን የሕብረት ሥራ ማኅበር እና ግለሰብ አባል ሊሆን ይችላል።

፮· *የኅብረት ሥራ ሊግ አመሠራረት*

፩) የዚህ እና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ ኅብረቶችና ፌዴሬሽኖች በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ማኅበራትን የሚወክል ሊግ ሊመሠርቱ ይችላሉ።

4/ "Appropriate Authority" means Cooperatives Commission established pursuant to article 2(1) of proclamation 274/2002 and includes cooperative promotion Bureaus and offices established in each region.

5/ "Union" means a union composed of more than one primary cooperative socieities that have similar objecties.

6/ "Federaton" means a group consists of unions and cooperative socieities with similar objectives

7/ "League" means cooperative society league of Ethiopia established by cooperative societies at the national level.

## SECTION TWO
## *Establishment of Cooperative Societies*

3. *Establishment of Primary Cooperative Societies*

1/ Primary cooperative society shall be established by voluntary individuals who live or work in the same area or engaged in the same profession. Number of members establishing the society shall not be less than ten. The appropriate authotiry shall, taking into account the economic efficiency, determine the least number of establishing members through directives issued by itself.

2/ The operational area of primary cooperative society established pursuant to article 1 of this article may be confined to one region or cover more than one regions.

3/ Different kinds of primary cooperative societies may be established in the operational area indicated in sub article 2 this article.

4. *Establishment of a union*

1/ Subject to the provision of this Regulation and that of other relevant laws on coperative society, primary cooperative societies having similar objective may establish a union.

2/ Subject to the Provision of this Regulation and that of other laws an individual who carries out similar activities to that of a union and who is willing to observe the principles of the society may become a member of the union.

5. *Establishment of Cooperative Federation*

1/ Subject to the provison of this Regulaton and that of other relevant laws, unions having similar objectives at Federal level may establish a Federation.

2) Subject to the provision of this Regulation and that of other relevant law, cooperative societies and an individual that carries out similar activities with that of the Federation may become a member of the Federation.

6. *Establishment of Cooperative League*

1) Subject to the provision of this Regulation and that of other relevant laws, primary cooperative societies, unions, and federations may establish a league that represents all cooperative societies in Ethiopia.

፪) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚመሠረት ሊግ ቁጥር ከአንድ ሊበልጥ አይችልም።

፯· <u>የሥራ ክልል</u>

፩) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ ወይም ፭ የተመሠረተ ማንኛውም ኅብረት ወይም ፌዴሬሽን የሥራ ክልል በኅብረቱ ወይም በፌዴሬሽኑ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይወሰናል ።

፪) የሊጉ የሥራ ክልል በአገር አቀፍ ደረጃ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተግባራትና ዓይነቶች</u>

፰· <u>የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተግባራት</u>

ማናኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር የማምረት ወይም አገል ግሎት የመስጠት ወይም የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ተግባራት ሊኖሩት ይችላሉ ።

፱· <u>የማምረት ተግባር የሚያከናውን የኅብረት ሥራ ማኅበር</u>

የማምረት ተግባር የሚያከናውን የኅብረት ሥራ ማኅበር በማምረት ሥራ ላይ የተሰማራ ወይም ጥሬ ዕቃ ወደ አላቂ ዕ. የሚቀይር ወይም በከፊል የተሠሩትን ወደ አላቂ ምርትነት የሚቀይር ይሆናል።

፲· <u>የአገልግሎት ተግባር የሚያከናውን የኅብረት ሥራ ማኅበር</u>

የአገልግሎት ተግባር የሚያከናውን የኅብረት ሥራ ማኅበር ለአባላት የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ወይም እንዲያገኙ የሚያደርግ ይሆናል ።

፲፩· <u>የማምረትና የአገልግሎት ተግባር የሚያከናውን የኅብረት ሥራ ማኅበር</u>

የማምረትና የአገልግሎት ተግባር የሚያከናውን የኅብረት ሥራ ማኅበር በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፱ እና ፲ የተመለከቱትን ተግባራት በጣምራ የሚያከናውን ይሆናል ።

፲፪· <u>የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓይነቶች</u>

፩) የተለያዩ የኅብረት ሥራ ዓይነቶች ሀገሪቱ በሚኖራት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የሥራ ዘርፎች ውስጥ ሊደራጁ ይችላሉ።

፪) የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓይነቱኛ መለያ ባሕሪያቸው፣ በሚሠሩት የሥራ አካባቢ ፣ በአመሠራረታቸው፣ በተግባ ራቸውና በሚኖራቸው የሕጋዊ ሰውነት የሚለይ ይሆናል።

፫) ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓይነቱኛ ባሕሪያት አግባብ ያለው ባለሥልጣን መመሪያ ያወጣል።

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ምዝገባ እንቅስቃሴ</u>

፲፫· <u>ምዝገባ</u>

፩) ሊጉን እና ፌዴሬሽኑን ጨምሮ በብሔራዊ ደረጃ የሚቋቋ ሙትን ዩኒየኖች የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ይመዘግባል።

፪) በዚህ ደንብ መሠረት የተመዘገበ ማንኛውም ማኅበር ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ሕጋዊ ሰውነት ያገኛል።



2) The number of the league establsihed pursuant to sub article 1 of this article may not exceed one.

7. *Operational Area*

1) The operational area of a union or a Federation Established pursuant to Article 4 or 5 of this regulation shall be determined by the by-laws of the union or the Federation.

2) The league shall have an operational area through out the territory of Ethiopia.

## SECTION THREE
## Types and Functions of Cooperative Societies

8. *Functions of Cooperative society*

A cooperative society may engage in production or service rendering activities or in both production and service rendering activities.

9. *Cooperative Society Engaged in Production Activities*

Cooperative Societies Engaged in Production Activities shall be one which takes part in production process or which converts raw materials or semi-finished products to finishedd products.

10. *Cooperative Societies engaged in service rendering activities*

A cooperative society engaged in service rendering activities shall deliver various services to members or cause them to obtain the same.

11. *Cooperatives Societies Engaged in Production and Service rendering activities*

A cooperative society engaged in production and service rendering shall carry out both activities indicated under article 9 and 10 of this regulation.

12. *Types of Cooperative Societies*

1/ Cooperative Societies of different type may be organized in any economic or social sector of the country.

2) Cooperative societies differ from others based on their unique nature such as their working place, establishment, function and legal personality they have.

3) The unique nature of cooperative societies shall be determined by a directive issued by the appropriate Authority.

## SECTION FOUR
## *Registration of Cooperative societies*

13. *Registration.*

1) The Federal Cooperative commission shall register the league and the federations as well as unions at the national level.

2) Any society established pursuant to this regulation shall have legal personality as of the date of its registration.

፲፬· <u>የኅብረት ሥራ ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ ስለሚይዛቸው ዝርዝሮች</u>

በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡

(ሀ) የማኅበሩን ዓላማ ፡ የኅብረት ሥራ እሴቶችና መርሆች፡
(ለ) የማኅበሩን አስተዳደራዊ መዋቅር፤
(ሐ) የማኅበሩን የበጀት ዓመት፤
(መ) የማኅበሩን ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም፤
(ሠ) የማኅበሩን ብድር አወሳሰን፤
(ረ) አባላት ከማኅበሩ ሲለቁ፡ ሲሰናበቱ ወይም በሞት ሲለዩ ተፈጻሚ የሚሆን ሥርዓት፤
(ሰ) የማኅበሩ የስብሰባ ሥነ ሥርዓትና ለአባላት የሚሰጥ ማስታወቂያ፤
(ሸ) የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም ሌሎች ኃላፊዎች የሚቀጠሩበት፡ የሚመረጡበት ሥርዓት፡ ሥልጣንና ተግባራቸው እንዲሁም የሥራ ዘመናቸው፤
(ቀ) የማኅበሩ ሠራተኞች አስተዳደር፤
(በ) ልዩ ውሣኔና የምልዓተ ጉባዔ ውሣኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች፤
(ተ) የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ለማሻሻል ተፈጻሚ የሚሆን ሥርዓትን ማኅበሩ ሲከፈል፡ ሲፈርስ ወይም ከሌሎች ማኅበራት ጋር ሲዋሃድ ተፈጻሚ የሚሆን ሥርዓት፡
(ቸ) ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጉዳዮች።

፲፭· <u>የኅብረት ሥራ ማኅበር አባላት የዕጣ ሰርተፊኬት</u>

፩) ማንኛውም አባል ለገዛው ሙሉ የዕጣ መጠን ሰርተፊኬት ይሰጠዋል።
፪) የዕጣ ሰርተፊኬቱ በምስጢር የሚታተም ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ አለበት
   (ሀ) የማኅበሩ ስም፣ አድራሻና ዓርማ፤
   (ለ) ማኅበሩ የተመዘገበበት ቀንና የምዝገባ ቁጥር፣
   (ሐ) የዕጣ ሰርተፊኬት መለያ ቁጥር፣
   (መ) የአንድ ዕጣ ዋጋ፣
   (ሠ) የአባሉ ስም ፡ የአባልነት መለያ ቁጥር፣
   (ረ) የገዛው የዕጣ መጠንና ዋጋ፣
   (ሰ) ማኅበሩን ለመምራት ሥልጣን ያለው ሰው ፊርማ፣
   (ሸ) የማኅበሩ ማኅተም ፣
   (ቀ) ሰርተፊኬቱ የተሰጠበት ቀን ፣ ወርና ዓመተ ምህረት፣
፫) የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ዕጣ ከአንድ የማኅበሩ አባል ወደ ሌላ አባል ወይም ከአንድ የማኅበሩ አባል ወደ ሦስተኛ ወገን ሊተላለፍ አይችልም።

፲፮· <u>የኅብረት ሥራ ማኅበር አባላት ስለሚሰናበቱበት ሁኔታ</u>

፩) ግዴታውን ያልተወጣ አንድ አባል ከማኅበሩ ይሰናበታል። አባሉ ግዴታውን እንዳልተወጣ የሚቆጠረው፤
   (ሀ) በተወሰነው የጊዜ ገደብ የዕጣ ክፍያን ያላጠናቀቀ እንደሆነ ፣
   (ለ) በማኅበሩ በሚሰጠው የሥራ ዘርፍ ከሁለት ጊዜ በላይ ግዴታውን ያልተወጣ ፣
   (ሐ) ማኅበሩ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ወይም ግብይቶች ለአንድ ዓመት ያልተሳተፈ ፣



14. *Particulars of by-laws of a Coöperative society*
Subject to the provision of article 11 of the Proclamation, any by-law of a cooperative society shall contain the following particulars:
(a) Objecties, values and principles of cooperative societies;
(b) Administrative structure of the society;
(c) Budget year of the soeiety·
(d) Manner of keeping the fund of the socieity and ways of its utilization;
(e) Procedures on loans;
(f) procedure to be applied in the instance of withdrawal, dismissal or death of members;
(g) Rules of procedures for the meeting of the society and notifications to be given to members;
(h) Procedures for the appointment or employment of managers and other officers of the society, their powers and duties and term of office;
(i) Administration of employee of the society;
(j) Matters requiring special or quorum resolutions (decision);
(k) Procedure to be applied in cases where the by-law of the society is amended or in cases where the society is dissolved, divided or amalgamated with other societies;
(l) Other appropriate particulars;

15. Share certificate of members of a cooperative society
1) Any member shall be granted certificate for the amount of full shares he has paid for.
2) The share certificate shall be printed in confidence (secretly) and shall contain the following particulars:
   (a) Name, address and emblem of the society;
   (b) Date of registration and registration number of the society;
   (c) Identification number of share certificate;
   (d) par value of each share;
   (e) Name and identification number of the member;
   (f) The amount of shares he has paid for (bought) and the price of the share he has bought;
   (g) Signature of a person entrusted with a power of leading the society;
   (h) Seal of the society;
   (i) Date, month and year of issuance of certificate;
3) The share of the society may not be transferred from one member to the other or from a member to a third party.

16. *Dismissal of members*
1) A member who failed to meet his obligation shall be dismissed from the society. The member shall be deemed not to meet his obligation where he:
   (a) has failed to pay fully for the shares within a period specified,
   (b) has failed to meet his oblitation emanated from the occupational sector granted by the society for more than two times;
   (c) has not participated for a year in any transaction or services rendered by the society;

(መ) ያለበቂ ምክንያት ለሁለት ተከታታይ ጊዜ በመደበኛ ስብሰባዎች ላይ ይልተሳተፈ እንደሆነ ነው።

፪) ጥፋት የፈጸመ አንድ አባል ከማኅበሩ ይሰናበታል። አባሉ ጥፋት እንደፈጸመ የሚቆጠረው፣

(ሀ) ከማኅበሩ ዓላማ ጋር የሚጻረር ተግባር የፈጸመ፣

(ለ) በማኅበሩ ንብረቶች ላይ ሆነ ብሎ አደጋ ያደረሰ ወይም እንዲደርስ ያደረገ፣

(ሐ) በተለያየ ምክንያት በእጁ የገባውን የማኅበሩን ንብረት ለግል ጥቅሙ ያዋለ፣

(መ) የማኅበሩን ገንዘብ ሆነ ብሎ ያጎደለ ወይም ሁኔታዎችን ያመቻቸ፣

(ሠ) በማኅበሩ ስም መደለያ ወይም ጉቦ የሰጠ ወይም የተቀበለ፣

(ረ) በማኅበሩ የሚገዙ ወይም የሚሸጡ ንብረቶችን ጥቅም ለማግኘት ሲል ከገበያ ዋጋ በታች የሸጠ ወይም ከገበያ ዋጋ በላይ የገዛ ወይም እንዲሸጥ ወይም እንዲገዛ ያደረገ፣

(ሰ) ለማኅበሩ የሚያቀርበውን ምርት ወይም አገልግሎት ዋጋ እንዳያገኝ ጥራቱን ያጓደለ ወይም መጠኑን የቀነሰ እንደሆነ ነው ።

፲፯· ስለ ክፍያ

ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር የምስክር ወረቀት ለማውጣት ወይም ምትክ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ ላይ የተመለከተውን ክፍያ ለመንግሥት ይከፍላል ።

፲፰· ምትክ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

፩) የተሰጠው የምስክር ወረቀት የጠፋበት ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር ምትክ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው አግባብ ያለውን ባለሥልጣን ሊጠይቅ ይችላል ።

፪) አግባብ ያለውን ባለሥልጣን ጥያቄው በቀረበለት በ፲ ቀን ጊዜ ውስጥ ምትክ የምስክር ወረቀቱን ይሰጣል ።

፫) አግባብ ያለው ባለሥልጣን ስለ ምትክ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

፲፱· ምዝገባ ስለሚከለከልበት ሁኔታ

ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር፣

፩) አስቀድሞ ከተመዘገበ ማኅበር ጋር ተመሣሣይ ስምና ዓርማ ያለው ከሆነ፣

፪) የራሱ የሆነ የፕሮጀክት ጥናት የሌለው ከሆነ፣

፫) በዚህ ደንብ እና በአዋጁ መሠረት ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ያላሟላ ከሆነ፣

፬) ዓላማው ይህን ደንብ ፣ አዋጅ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን የወጡ መመሪያዎችን የሚፃረር ከሆነ፣ ተመዝግቦ የምስክር ወረቀት ማግኘት አይችልም ።

## ክፍል አምስት

## ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበሩ ስብሰባዎች

፳ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ

፩) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ያደርጋል።

፪) ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

(d) Has not participated in two consecutive regular meetings of the society without sufficient reason.

2) Any member who has committed a fault shall be dismissed from membership. The member shall be deemed to have committed a fault where he has;
   (a) Committed a fault which is contrary to the objective of the society;
   (b) Deliberately caused harm or caused to be harmed the properties of the society
   (c) Misappropriate the properties of the society that he has received for various reason;
   (d) Deliberately misappropriate the fund of the society or facilitate conditions for the same action to be committed;
   (e) Bribed somebody or been bribed by somebody in the name of the society;
   (f) Sold or caused to be sold under price or bought or caused to be bought over price the properties of the society with view to derive unlawful advantage;
   (g) Reduced the amount or the quality of product or service that the society supplies.

17. *Charges*

Any cooperative society shall pay charges indicated in the schedule attached thereto to government upon receiving a share certificate or its substitute.

18. *Grant of substitute certificate*

1) A cooperate society that has lost its certificate may apply to appropriate authority for the grant of substitute certificate;
2) The appropriate authority shall grant the substitute certificate within 10 days as of the submission of the request.
3/ The appropriate authority shall issue directives on the manner of granting substituted certificate;

19. *Conditions for the Prohibition of Registration*

Any cooperative society shall not get registered and be granted certificate where:
1) It has got similar name and emblem with the society that has already registered;
2) It lacks its own project proposal;
3) It doesn't observe registration requirements specified in this regulaton and the proclamation;
4) Its objective is found contrary to this regulation, the proclamation and directive issued by the appropriate authority.

## SECTION FIVE

## *Meetings of a Cooperative society*

20. *Regular Meeting of the general Assambly*

1) Any cooperative society shall convene its regular general assembly at least once in a year.
2) There shall be a quorum where more than half members of the general assembly are present.

፫) መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ተጠርቶ ምልዓተ ጉባዔው ካልተሟላ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ይጠራል ። ለሁለተኛ ጊዜ የተጠራው መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በተገኙት አባላት መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ይካሄዳል።

፬) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ምልዓተ ጉባዔ ሳይኖር የተካሄደ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚያሳልፋቸው ውሣኔዎች ሁሉም የጉባዔው አባላት በተገኙበት እንደተላለፈ ይቆጠራል።

፳፩· አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ

፩) በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ መሠረት የተጠራው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዓተ ጉባኤው ካልተሟላ በ፲፭ ቀናት ውስጥ የሥራ አመራር ኮሚቴው ለሁለተኛ ጊዜ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ይጠራል። ለሁለተኛ ጊዜ የተጠራው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጥሪ የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል ።

፪) ከጠቅላላው አባላት ሁለት ሦስተኛው ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል ።

፳፪· ጥሪ ስለማድረግ

በዚህ አዋጅ መሠረት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ከመደረጉ ከ፲፭ ቀን በፊት የማኅበሩ የሥራ አመራር ለአባላቱ ሀገር አቀፍ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም አመቺ ሆኖ በተገኘው መንገድ ጥሪ ማድረግ አለበት።

፳፫· የሕብረት ሥራ ማኅበር የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት

፩) በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በቀር በመደበኛ ወይም በአስቸኳይ ጉባዔው የሚተላለፉ ውሣኔዎች በአባላቱ የአብላጫ ድምጽ ይሆናል ።

፪) የድምጽ አሰጣጥ እኩል በኩል የተከፈለ ሲሆን የጉባዔው ሰብሳቢ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል ።

## ክፍል ስድስት
## ስለ ሕብረት ሥራ ማኅበር ንብረትና ገንዘብ

፳፬· የተጣራ ትርፍ አደላደል

፩) ከማኅበሩ የተጣራ ትርፍ ላይ ፴ በመቶ እየተቀነሰ በመጠባበቂያ ሂሣብ ይቀመጣል ። የመጠባበቂያ ሂሣቡ የሚቀመጠው ከማኅበሩ ካፒታል ፴ በመቶ እስከሚደርስ ብቻ ነው።

፪· በየዓመቱ ከማኅበሩ የተጣራ ትርፍ ውስጥ እየተቀነሰ በመጠባበቂያ የሚመደበው ገንዘብ በማኅበሩ ስም የቁጠባ ሂሣብ ተከፍቶለት ይቀመጣል ። ስለአጠቃቀሙ አግባብ ያለው ባለሥልጣን መመሪያ ያወጣል ።

፳፭· ስለሕብረት ሥራ ማኅበር የማይከፋፈል ንብረት

ማንኛውም የማኅበሩ ንብረት፣

(ሀ) በመጠባበቂያ ሂሣብ ውስጥ የተመዘገበ ከሆነ፣

(ለ) በስጦታ ወይም በውርስ የተገኘ ከሆነ የወል ንብረት ይሆናል ።

፳፮· የሕብረት ሥራ ማኅበር ሲፈርስ ስለሚኖረው ንብረት አከፋፈል

ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር በሕግ መሠረት ሲፈርስ በአዋጁ አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት ሕብረት ሥራ ሉ ማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ተከፍሎ የሚቀረው ንብረት ሕብረት ሥራ ማኅበሩ ሲፈርስ ለነበሩ አባላት ፣ ሕብረት ሥራ ማኅበሩ ከመፍረሱ በፊት ያለጥፋት ለተሰናበቱ አባላትና ለሟች አባላት ተተኪዎች እንደየድርሻቸው ይከፋፈላል። ስለአከፋፈሉ አግባብ ያለው ባለሥልጣን መመሪያ ያወጣል ።

3. Where there is no quorum of the general assembly called, the second general assembly shall be called within 15 days as of the date of the first general assembly. Where there is no quorum for general assembly called for the second time, the meeting shall be convenced by members present.
4. The decision passed by the general assembly, which is convenced in a situation where there is no quorum as is indicated in sub article 3 of this article, shall be deemed to have been made in the presence of all members.

21. *Emergemcy meeting of the General Assembly*
    1. Where there is no quorum in an emergency meeting called as per article 22 of the proclamation, the managment committees shall call the second emergency meeting within 15 days as of the date of the first meeting. Where there is no quorum in emergency meeting called for the second time, the appropriate authority may call another meeting.
    2. There shall be quorum where two third of members of the general assembly are present.

22. *Call for the meeting*

    The managment committee shall make a call, as per the provisions of the proclamation to all members 15 days before the emergency meeting is convened through a News Paper having nation wide circulation or using any means found convenient.

23. *Voting Procedure of a Cooperative society*
    1) Unless and otherwise provided in the by-law of the society, decision of regular or emergency meeting shall be passed by a majority vote.
    2) In cases of a tie, the chairperson of the general assembly, shall have a casting vote.

## SECTION SIX
### *Assets and funds of the Cooperative society*

24. *Allocation of Net profit*
    1. 30% of the net profit of the society shall be deducted and allocated for the reserve fund. The amount allocated for the reserve shall be deposited only until it shall not exeed 30% of the capital of the society.
    2. The amount of fund deducted from the net profit and allocated for the reserve shall be deposited in a saving account opened in the name of the society. The utilization/aplication of this fund shall be determined by directive issued by appropriate authority.

25. *Indivisibility of Assets of the society*

    Where the asset of the society is:

    (a) Registered as a reserve fund account.

    (b) Obtained through donation or inheritance it shall remain indivisible and common asset of the society.

26. *Distribution of Assets of Dissolved Cooperative society.*

    The assets of a dissolved cooperative society left after the creditors are paid as is indicated under Article 44 sub article 4 of the proclamation shall be distributed to a member who is active at the time when dissolution pronounced, to a member who is dismissed for the reason other than committing a fault, and to a substitute of a deceased member. Manner of distribution of the asset shall be determined by a directive issued by the appropriate authority.

፳፯. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ ተፈጻሚነት የለውም።

፳፰. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

አግባብ ያለው ባለሥልጣን ይህን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል ።

፳፱. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኅብረት ሥራ ኮሚሽን

የምስክር ወረቀት አገልግሎት ክፍያ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የምስክር ወረቀቱ ዓይነት | የክፍያ መጠን/ብር | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ ምዝገባ | 60 | |
| 2 | ምትክ | 30 | |
| 3 | ጊዜያዊ | 30 | |

27. *Repealed laws*

Regulations or a directives inconsistent with this regulation shall be inapplicable.

28. *Power to issue a Directive*

The appropriate authority shall issue a directive necessary for the implementation of this regulation.

29. *Effective Date*

This regulation shall come in to force on the date of its publication in the Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 28th day of June 2004

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

The Federal Democratic Republic of Ethiopia

Cooperative Commission

Schedule of fees for certificate service

| No | DESCRIPTION | FEE/BIRR | REMARK |
|---|---|---|---|
| 1 | NEW REGISTRATION | 60 | |
| 2 | SUBSTITUTION | 30 | |
| 3 | TEMPORARY CERTIFICATE | 30 | |

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት